# ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ
# ነጻነት

ነጻነት ሰው የመሆን መሠረታዊ ባሕርይ ነው፣ ነጻነት የሌለው ሰው ከእንስሳት የሚሻል አይሆንም። የሰው ልጅ እንደእንስሳት ጉልበት አለው፣ በተጨማሪ ደግሞ አእምሮ አለው፣ህሊና አለው። ነጻነት በሌለበት አእምሮና ህሊና ቀርቶ ጉልበትም ይዶለድማል።

ነጻነት ስንል ምን ማለታችን ነው? ሰው አእምሮ አለው፣ ስለዚህም ያስባል። ማሰብ ትልቅ ኃይል ነው፣ ለሰው ልጅ ትልቁና ዋናው መሣሪያው የማሰብ ችሎታው ነው፣ ማናቸውም የሰው ልጅ ሥራ ሁሉ የሚያስብ አእምሮ ውጤት ነው። ማሰብ ኃይል የሚሆነው በነጻነት ነው፣ ማሰብ ሥልጣን ሚሆነው በነጻነት ነው፣ ነጻነት የራስ ባለቤትነትና ራስን መቻል ነው። የሰው ልጆች በሥልጣኔ ደረጃ የተለያዩበት ምክንያት የሠለጠኑት አእምሮ ስላላቸውና ያልሠለጠኑት ደግሞ አእምሮ ስለሌላቸው አይደለም።

ልዩነታቸው አእምሮአቸውን እንደመሣሪያ በመጠቀማቸውና ባለመጠቀማቸው ላይ ነው። የሠለጠኑት አእምሮአቸውን በሙሉ ኃይሉ ይጠቀሙበታል፣ ፍርኀትና ጭንቀት በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው የእወቀትን አድማስ እየገፉና እያሰፉ፣ አዳዲስ ነገሮችን እየፈጠሩ ወደሰማየ ሰማያት መጥቀው፣ ጠጣሩን መሬት ሰንጥቀው ውቅያኖሶችን ጠልቀው፣ ጥቃቅን ለዓይን የማይታዩ ህዋሳትን አጉልተውና የተሰወረውን ሁሉ ገልጠው እውቀትን በእውቀት ላይ ይክባሉ። እንዲህ የአእምሮ ኃይላቸውን በልበ ሙሉነት እንዲጠቀሙበትና እንዲያጎለብቱት የሚያደርጋቸው ነጻነት ነው።

በአንፃሩ ነጻነት በሌለበት ማሰብ አደገኛ ተግባር ነው፣ ለአገር በሙሉ የሚበጀውን የምናውቀውና የምናስበው እኛ ብቻ ነን ብለው የሚያስቡ ሰዎች እሺ ብሎ ትእዛዝ የሚቀበል እንጂ ሚያስብና ሽንጡን ገትሮ የሚከራከራቸው ሰው አይወዱም። ስለዚህም የሌሎች ሰዎች አእምሮ ሽባ እንዲሆን ጫና ይደረጋል፣ ብዙኃኑ በጭቆና ተሰንጎ፣ በፍርሃትና በጭንቀት ደንዝዞ፣ በደህነትና በረሀብ ተዋርዶ፣ አእምሮውንና ኅሊናውን አስተኝቶ ለሆዱ ብቻ እንዲገዛ ይደረጋል። አእምሮ ሲታፈን ጉልበትና ኅሊናም ይዳከማሉ። ገዢዎች ደህ ማሰብ ከጀመረና ከጠገበ አይገዛም ብለው ይሰጋሉ። የኋላ ቀርነት መሠረቱ ይህ ነው። ጨቋኞች መጨቆንን እየለመዱ፣ ተጨቋኞችም ጭቆናን እየለመዱ ጭቆና ባህል ይሆናል።

ለራሱ ሲሆን ጨቋኙም ነጻነትን አይጠላም፣እንዲያውም ጨቋኙ ለነጻነት ያለው ፍላጎት ፍጹም ነው፣ ጨቋኙን ጨቋኝ የሚያደርገው ብቻውን የሙሉ ነጻነት ባለቤት መሆኑ ነው። እሱ የሚፈልገው ነጻነት በእግዚአብሔር፣ በኅሊና፣ በይሉኝታ፣ ወይም በሕግ ያልተገራና ያልተገደበ መሆን አለበት። እንደልብ ለመጨቆን ያልተገደበ ነጻነት ያስፈልጋል።

ነጻነቱን የተገፈፈ ሰው በማናቸውም ደረጃ ለጥቃት የተጋለጠ ይሆናል፣ ለዚህ ነው በግለሰብ ደረጃ የልጅዋ ረሃብ ሰቀቀን ሆኖባት በመንገድ ዳር ቂጣ ወይም ድንች የምትሸጥ እናት፣ የዕለት እንጀራ ለማግኘት ጥቃቅን ነገሮችን የሚይዝ ሱቅ በደረቴ ወጣት፣ ጋዜጣ በየመንገዱ እየተዘዋወረ የሚሸጥ ልጅ የሚቸገሩትና የሚዋከቡት። ለዚህ ነው በማኅበራት ደረጃ የከተማ ቀበሌ፣ የገጠር የገበሬ ማኅበራት፣ የሠራተኞች ማኅበራት፣ የወጣቶችና የሴቶች ማኅበራት በካድሬዎች ታፍነው ወይም ተከፋፍለው ፋይዳ ያለው ነገር ለአባሎቻቸው ለመሥራት ያልቻሉት፣ ለዚህ ነው የመምህራን ማኅበር ከነአባሎቹ ፍዳውን የሚበላው፣ ለዚህ ነው አንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበርና የነጻ ጋዜጠኞች ማህበር በተለጣፊዎች ተወጥረው እንዲያዙ የተደረጉት። ለዚህ ነው ሥርዓቱ መጠርነፍ (አጋብሶ ማሰር) የሚባለውን ቃል በተግባር የሚያውለው። መጠርነፍ የአፈና ሥርዓት መግለጫ ነው።

አንድ የታወቀ የእንግሊዝ ፈላስፋ ሰዎችን አፍኖና ነፃነትን ነፍጎ መግዛት ሰዎቹን ያሳንሳቸዋል፣ስለዚህም ለጊዜው ፀጥ ለጥ ብለው መገዛታቸው ለገዢዎቹ ቢመችም ትልቅ ሥራ በትንንሽ ሰዎች እንደማይከናወን ሊያውቁት ይገባል፣ ይላል። ሰዎችን ነጻነት መንፈግ ከባሕርያቸው በታች ማውረድ ነው፣ እንኳን ለአገርና ለወገን ለራሳቸውም ማሰብ የሚያቅታቸው ይሆናሉ። ጊዜያዊ የግል ጥቅም የዘለቄታውን የራሳቸውንና የልጆቻቸውን ጥቅም እንዲረሱ ያደርጋቸዋል፣ በአመራርም ይሁን በመሣሪያነትም ይሁን ነጻነትን የሚያፍኑ ሁሉ አውቀውትም ሁነ ሳያውቁት ሥራቸው ቆይቶም ቢሆን የሚያስከትለው ከባድ ጉዳት በራሳቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በልጆቻቸውም ላይ ነው። ተንጋልሎ የተፋ ለራሱ ከፋ እንደሚባለው ነው።

አእምሮ የሚደላውና ነቅቶ የሚሠራው በነጻነት ነው፣ አእመሮ ሴደላው ብዙ ትልልቅ ነገሮችን ያስባል፣ አዳዲስ ሥራዎችን ይፈጥራል፣ አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን ያፈልቃል፣ ሀብት የሚከማቸውና ኑሮ የሚመቸው በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ነው። የአእምሮ ውጤቱን ተቀብሎ በሥራ ላይ የሚያውለውም የእጅ ብልሃት ያለው ሰው

ነጻነት ያስፈልገዋል፡፡ የሚሸጠውም፣ የሚቸረችረውም፣ የሚገዛውም ነጻነት ያስፈልገዋል፡፡

ነጻነት ከሰው ሰብአዊ ክብር የሚመነጭ የሰብአዊነቱ መገለጫ ክስተት ነው፡፡ በተለያዩ የአለም ክፍሎች ያሉት ህዝቦች የሚያስተሳስራቸው አንድ ታላቅ ሃይል ቤኖር፣ ለነፃነት ያለ ጥማት ነው ፡፡ የነጻነት ጥማት ያደረበት ህዝብ ህልማዊ ሥዕል ያስፈልገዋል፡፡ ፈላስፋው እንዳለው "ከሩቅ የሚታይ የውበት ሥዕል ያሻዋል፡ ያን ጊዜ ከኋላው የሚገፋው አያስፈልገውም፡፡ እራሱ በገዛ ተምኔቱ እየተሳበ፣ እየተጉተተ ይቀርባል፡፡ ያንን የውበት ዕቃ ለመማረክ፣ ለመጨበጥ የራሱ ለማድረግ ይጥራል፡፡ እዚያ ካልደረሰ ዕረፍት የለውም ሰላም ያጣል ጸጥታም አያገኝም፡፡ ቀን ያስባል፣ ያቅዳል፣ ይሠራል፡፡ ሌሌት ያልማል ይባንናል፡፡ ይህም የምኞቱን ሕልማዊ ሥዕል እውናዊ ለማድረግ ነው፡፡"

ቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ በእንዲህ ዐይነት የነፃነት ምኞትን ህልማዊ ሥዕል እውናዊ ለማድረግ በሚቧትቱ የሠላም ታጋዩች የተቀናጀ ሃይል ነው፡፡ ነፃነት በታምራት፣ በድግምት፣ ወይም በምትሐት የሚገኝ ሳይሆን፣ ሰው በገዛ ህሊናው ጉልበት፣ በዕውቀት የሚደርስበት የአድካሚ ጉዞ ውጤት ነው፡፡ ፈላስፋው እንደተናገረው "ሰው በዕውቀት እየበለፀገ ሄዷል ወትሮ ደሃ ነበር፡፡ ከዚህ ደረጃ ያደረሰው ይህ ህሊናው እንደተረሳ ምንቸት በተረት ጥረሾ ታጅሎ የተፈጥሮ ችሎታውን ባለማወቅ ሰው በዙሪያው የሚገኙት የሥነፍጥረት ጉልበቶች መጫወቻ ሆኖ ነበር ፡፡ ዓለምን እንደ አንድ ትንሽ ዛኒጋባ በመረዳት ራሱን ቀና ቢያደርግ ጣሪያው፣ እጁን ቢዘረጋ ግድግዳው የሚመታው እየመሰለው ባለበት ቦታ መንፈሱ ተኮራምቶ ለብዙ ዘመናት በችግር ኖሮአል፡፡ "

"ችግር አንድ ደግነት አለው፡፡ የዕውቀት ምንጭ ነው፡፡ በጣም የተቸገረ ሰው ግራ ይገባዋል፡፡ አእምሮው ይጨልማል፡፡ "በአምጣነ ጽልመታ ከማሁ ብርሃና» ሕሊና ከጭለማ ከጽልመት ጋር በታገለ መጠን ያንኑ ያህል ብርሃን ያገኛል፡፡ የሰው ልጅ ታገለ ከሕሊናው ብርሃን ሠረፀ፡፡ የእውቀት ጐዳና ታየው፡፡ ወደላይ ተጓዘ፡፡ ከከፍተኛ ቦታ ደረሰ፡፡ አርቆ ለማየት ቻለ፡፡ ተደሰተ፡፡ ጥረቱን ቀጠለ፡፡ ይህንን የድል ጎዳና የቀደዱ ብዙዎች የመንፈስ ማሃንዲሶች ናቸው፡፡"

ኢትዮጵያዊው ሰው ከዘመናዊ ትምህርት፣ ለንግድ በተሰማራባቸው ሃገሮች በታዘበው፣ በስደት ህይወቱ፣ ከቀመረው ይሄንን የሰው ልጅ ከሕሊናው ያሠረፀውን ብርሃን ሲሻ ሶስት ግማሽ ምዕተ አመታት አሳልፏል:: ከቴዎድሮስ ትንሳኤ እስካለንበት ደቂቅ ያለው ተጋድሎ ኢትዩጵያውያን ወደ ዘመናዊ ህይወት ብሎም ወደተሟላ ነፃነት ለማሻቀብ፣ የሞት ሽረት ትግል ያካሄዱበት ዘመናት ናቸው:: ሃገራዊ ነፃነትን ከውጪ ወራሪዎች ከመከላከል አንስቶ እስከ ማኅበራዊ ነፃነት መሻት ድረስ የተደረገት ፀረ ጭቆና ተጋድሎዎች የዚሁ የነፃነት ጥማት ውጤቶች ናቸው:: የነፃነት ጥማት ያደረባቸው የየዘመኑ ኢትዮጵያዊያን ከነበሩበት የኑሮና የሃሳብ ዘዴ ወጥቶ የገዛ ሕሊናውን መርምሮ ባስገኘው ሕግ ኑሮውን እንዲመራ ለማነሳሳት ያደረጉት ትግል ከባድ ፈተናዎችን ማለፍ ነበረበት:: አሮጌውን ትቶ አዲሱን እስኪጨብጥ ድረስ ኢትዮጲያዊው ሰው ባዶ እጁን ነበር:: በተለይ ባለፉት 30 ዓመታት አሮጌውን ትቶ አዲስ በመቀበል መሃል በነበረው ትግል የአንድ ትውልድ ሕይወት መክኗል:: ከአዲሱም ሆነ ከአሮጌው በደንብ ለመሳተፍ ባለመቻሉ የሚመጣ ችግር ነው:: ያኛው አሮጌ ነው ተብሎ ይተዋል ዘመናዊው ደግሞ ገና ብዙዎቹ ያልተቀበሉት ስለሆነ ደግሞም ብዙ ጥረት እና ድካም ስለሚጠይቅ ችላ ይባላል::

በእንዲህ ያለ ዘመን ይላል ፈላስፋው " በመንፈስ ከሁለቱም ያጣ ሆኖ የመቅረት አደጋ ይደርስበታል" በእንዲህ ያለ ዘመን የሚኖረው ሰው በሁለቱ መካከል በአዲሱና በአሮጌው ወዲያ እና ወዲህ ሲንከራተት በመጨረሻ ይሰለቸውና የመንፈስን ጥረት ረስቶና ዋጋ እንደሌለው ቆጥሮ ተምኔቱ ወደ ሌላ እንደ ጥቅም ወደ አሉ ነገሮች ወደ ሃብት ንብረት ያዘነብላል:: የመንፈሱን ችግር በዚያ ለመደለል ይጣጣራል:: ያን ጊዜ ግሩም የሆነ የሰው ጠባይ ይፈጠራል:: ጥልቅ ሃዘን ንፁህ ደስታ አያውቅም፣ አያምንም፣ አይክድም፣ ምርር ብሎ አያለቅስም፣ ፍንድቅ ብሎ አይስቅም:: ጠላት የለውም ወዳጅ የለውም ቁርጥ ሃሳብ ለሚጠይቁ ነገሮች ሁሉ ግዑዝ ገለልተኛ ማዕከላዊ ሆኖ ይገኛል:: ለታላላቅ የህይወት ችግሮች የግዴለሽነት አስተያየት ይኖረዋል::

" በእንደዚህ ዓይነት ሰዎች መካከል አርቆ የማየት ኃይል ያላቸው የተመረጡ መናፍት ይገኛሉ:: «ኀሩያን ኀዳጣን» ጥቂቶች ናቸው ግን የህሊናቸው ሰለት የደረታቸው ግለት መሰናከሉን ሁሉ ቆርጦ ሁለቱን ስልጣኔዎች በዝምድናቸው መሰረት ለማገናኘትና ለማስተዋወቅ በመጨረሻም ለማዋሀድ ይጥራሉ:: ጥረታቸውም ይከናወናል:: በመጀመሪያ የገዛ ራሳችንን ደህና አድርገን ማላመጥ መዋጥ፤ ቀጥሎም ከውጭ የመጣውን በዚሁ መንገድ አሳልፎ መደባለቅ ማዋሃድ:: ያንጊዜ ከሁለቱ የሰረፀ በገዛ ወዛችን የተጥለቀለቀ አዲስ የመንፈስ ህይወት ይታያል::

ባለፉት ሰላሳ አመታት ባሳለፍናቸው ምስቅልቅል የለውጥ ሂደቶች፣ከነብረሰብአዊነት እስከ ነጭ ካፒታሊዝም በተፈከሩ ሙከራዎች መሃል ግራ የመጋባት፣ ከዳር ቆሞ የማየት፣ ምርር ብሎ አለማልቀስም ሆነ ፍንድቅ ብሎ ያለመሳቅ፣ ግዑዝ ገለልተኛ አስተያየትም የመያዝ አዝማሚያዎች ተጠናክረው መታየታቸው ገሀድ ነው። ባንጻሩም፣ ነፃነት የሌለበት ህይወት ባርነት ነው ብለው ያመኑ፣ ለግለሰብ ነፃነት የሚከፈለው መስዋትነት ተገቢ ነው ብለው የተቀበሉ የጧፍ መብራቶች በተለይ ባለፉት 14 አመታት ተከስተዋል። መንግስት መኖሪያ ቤታቸውንና ቢሮአቸውን እንዲፈተሽ፣ ሀገር ቤት ሲገቡ ወደ እስር መወርወር እንደሚጠብቃቸው እያወቁ፣ ለነፃነት የሚከፈል መስዋዕትነት ተገቢ ነው ብለው ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በእስር የማቀቁ ዜጎችንም ኢትዮጵያ አፍርታለች። የሰላም አርበኞች ቀፍቅፋለች። ይህም መስዋዕትነትና ገድል፣ እንዲሁ መክኖ አልቀረም። ህዝቡ ለነፃነቱ ቀናኢ እየሆነ፣ የመምረጥ መብቱን ቁልፍነት እየተረዳ፣ ከራሱ አመኔታ ውጪ የሚጫን ምንግስታዊ ስልጣን ህገወጥ መሆኑን ያበሰረ፣ የ 14ቱን አመታት የአገዛዝ ስርአት በሩን በረግዶ እንዲከፈትና የህዝቡን እሮሮ እንዲያደምጥ የሚያስችል በቂ ግፊት በማድረግ ላይ ይገኛ ል።

ይህ የነፃነት ግፊት ጉልበቱን ይበልጥ እያሰባሰበ በነጎደ ቁጥር፣ ሌሎች የበለፀጉ ህዝቦች ለመንደርደር የሚያስችለንን የነፃነት ጎዳና ለመያያዝ እንችላለን። የነፃነቱ ግብ ግን ከግንቦት ሰባቱ ምርጫ ጋር የተቆላለፈ ነው። ህዝቡ ለ14 አመታት ያየውን የኢህአዴግ ውድቅ አስተዳደር፣ ይገባኛል ብሎ በሚመኘው የነፃነት ስርአት ለመተካት ሲችል ነው በአሰተማማኝ መልኩ ጉዞውን የሚያገባድደው። ለዚህም ሰላማዊ የለውጥ አርበኞች የተሠለፉበትን፣ ከአራቱ አባል ድርጅቶቹ ከመኢአድ ፣ ከኢዲአፓ-መድህን፣ ከቀስተዳመና እና ከኢዴሊ የተወጣቱትን የቅንጅት እጩዎች በየምርጫው ወረዳው ሲመርጥና ይሁንታውን ሲገልፅ ነው ትግሉ ዕልባት የሚያገኘው። ቅንጅት ነፃነት ነው የምንለውም ለዚህ ነው።

ምርጫ አንዱ የነጻነት መግለጫ ነው፣ ማንንም ሳትፈሩ፣ በጊዜያዊ ጥቅም ሳትታለሉ፣ ለዘለቄታው ለእናንተና ለልጆቻችሁ ይበጃል የምትሎት ምረጡ፣ አምላክ እውነተኛውን መንገድ ያሳያችሁ። ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ማለት ልማት በነጻነት ማለት ነው።

ከቅንጅት ጋር ወደፊት!